# ወርሃዊ የአየር ጠባይ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦገስት 1-31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም

## ከሴፕቴምበር 1-30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር 2022
አዲስ አበባ

ርዕስ                                                                                                    ገፅ


እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ....................3

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....................5

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....................6

ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ....................7

ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....................7

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ....................8

ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....................8

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....................8

እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....................9

ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....................9

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ....................10

ጠባይ አዝማሚያ ....................10

ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....................11

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....................11

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....................12

## እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ


ባለፈው የኦገስት ወር በየጣልቃዉ ፀሃያማ ሁኔታ የተስተዋለበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም፤ ለወቅቱ ዝናብ መፈጠር መንስኤ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በመጠናከራቸዉ ጠንካራ እርጥበት አዘል አየር ወደ ሀገራችን ሲገባ ቆይቷል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ በአብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋና የተጠናከረ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡

በአጠቃላይ ባለፈዉ ወር በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች፣ በሰሜን ሶማሌ፣ በሐረሪና ድሬዳዋ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ በሲዳማና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም በአፋር እና በደቡብ ኦሮሚያ ጥቂት ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ባለፈው ወር አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በሃያ አራት ሰዓታት ዉስጥ እስከ 125.4 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በመጣሉ ቅፅበታዊ ጎርፍ በተለያዩ አካባቢዎች ላይ አስከትሏል፡፡ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ 30 እስከ 125 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ በብዙ ጣቢዎች ላይ የተመዘገበ ሲሆን፤ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በጎሬ 125.4፣ በአልጌ 40.0፣ በአርጆ 46.6 እና 40.2፣ በአሶሳ 42.3፣ በባቲ 52.0፣ በቻግኒ 63.2፣ በጨፋ 53.1፣ በኮምቦልቻ 45.0፣ በድሬዳዋ 98.7፣ በደባርቅ 58.8፣ በኢጃጂ 47.2፣ በጋምቤላ 109.0 እና 87.2፣ በጎንደር 42.7፣ በላሊበላ 65.4፣ በምዕራብ አባያ 66.0፣ በማጀቴ 59.9፣ በማሻ 40.2፣ በነጆ 47.1፣ በኑራኤራ 45.1፣ በሾላ ገበያ 50.0፣ በስሪንቃ 62.5 እና 51.4፣ በሻውራ 54.3፣ በወረኢሉ 59.9፣ በላሬ 50.5፣ በጊዳአያና 68.7፣ በጉንዶ መስቀል 52.8 እና 49.0 በወረኢሉ 60.9፣ በኢሊያይ 65.2ና 36.7፣ በአቦቦ 40.0ና 40.2፣ በባህርዳር 48.8 እና 60.4፣ በዳንግላ 41.5፣ በቡሬ 70.6 እና 51.0፣ በጊንቢ 45.6፣ በላሬ 82.0፣ በፉግኖዶ 49.0 እና 46.7፣ በሳዉላ 51.8፣ በማጂ 58.0 እና 53.0 እንዲሁም በዳሊፋጊ 48.2 በሚ.ሜ የገኙባቸዋል፡፡


ባለፈዉ የኦገስት ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከ25-483 ሚሜ የሚደርስ ዝናብ የወቅቱን ዝናብ ከማያገኙት ከደቡብና ከደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም ከቦረና፣ ከባሌና ከጉጂ ዞኖች በስተቀር በሁሉም የሀሪቱ ክፍሎች ላይ ከ5-30 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 7 እና 8) ፡፡

ባለፈዉ የኦገስት ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በትግራይ፣ በአፋር፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል-ጉመዝ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ሁሉም ዞኖች፣ በወለጋና ሸዋ ሁሉም ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በጅማ፣ በባሌና ጉጂ እንዲሁም በቦረና አንዳንድ ቦታዎች፣ በስልጤ፣ በጉራጌ፣ በሀዲያ፣ በሲዳማ አብዛኛዉ ዞኖች እንዲሁም በአዲስ አበባ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በተቀሩት የምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ የአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ የሲቲና ፋፈን ጥቂት ስፍራዎች ላይ ከመደበኛው ያነሰ የዝናብ መጠን ነበራቸው ( ካርታ 9)፡፡


ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 8   ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 9 ኢ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው የኦገስት ወር ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ የሆኑት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ረገድ ጥሩ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈርን እርጥበት ከማሻሻልና ተክሎች የሚያስፈልጋቸውን ውኃ ከማቅረብ አንጻር ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ከሰብል ልማት አንጻርም ቀደም ሲል በሚያዝያና በግንቦት ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙት የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት እንዲሁም በክረምት ወቅት ተዘርተው በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉት እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ እና ጤፍ ለመሳሰሉት የብርዕ ሰብሎች፣ የጥራጥሬ እህሎችና የቅባት እህሎች በተጨማሪ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም ባሻገር ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት መሟላት በጎ ጎን ነበረው፡፡ በተጨማሪም በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባድ ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ በዚህም ምክንያት የመሬት መንሸራተት፤ በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ባሉ ሰብሎች የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛትና ቅጽበታዊ ጎርፍ በተወሰኑ ቦታዎች በመከሰቱ በተለያየ የእድገት ደረጃዎች ላይ ባሉ ሰብሎች፣ በአፈር ጥበቃ ሥራ እንዲሁም በሰው እና በንብረት ላይ መጠነኛ ጉዳት ነበረው፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የነበረው ከባድ ዝናብ በአንዳንድ በሰሜን ምዕራብ፤ በመካከለኛዉና በምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የመሬት መደርመስና የወንዞች መሙላት በመከሰቱ በሰብሎች፤ በሰዎች እና በእንስሳት እንዲሁም በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ወር የተገኘው እርጥበት ቀደም ባሉት ጊዜ የእርጥበት እጥረት ለነበረባቸው ቆላማ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለሚኖሩት አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጥሩ አስተዋፅኦ ነበረው (ካርታ 10)፡፡


ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከኦገሰት1-31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በአገሪቱ በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብና በመካከለኛዉ እንዲሁም የደቡብና የምሥራቅ ከፍተኛ ቦታዎች የሆኑት ተፋሰሶች ላይ የተሸላ አርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው ተስተውሏል። ይህንን ሁኔታ ተከትሎ በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ እና ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል በጥቂት የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛው ገናሌዳዋ፣ አፋርደናከል፣ የታችኛው አዋሽ እንዲሁም የታችኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በመሆኑም ባለፊው ወር የተገኘው እርጥበት ለውሃ ሃብት ከፍተኛ ግብዓት ከመሆኑም በላይ በመጠን ረገድ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ በተከታታይ ከባድ ዝናብ በመኖሩ የወንዞች እና የውሃ ማጠራቀሚዎች ላይ የውሃ ሙላት ተከስቷል (ካርታ 11) ፡፡

ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ ሴፕቴምበር ለክረምት ወቅት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተዳከመና እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆነው የሰነበቱት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

የወቅቱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሴፕቴምበር ከመጀመሪያው አሥር ቀናት ጀምሮ ከሰሜን ምሥራቅና ከሰሜን ኢትዮጵያ ቀስ በቀስ እየተዳከመ ወደ ምዕራብ፤ ደቡብ ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በወሩ መጨረሻ ሳምንት ደግሞ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅና የመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች በበጋው ደረቅ የአየር ጠባይ ተጽዕኖ ሥር መሆን ይጀምራሉ፡፡

በመጪው የሴፕቴምበር ወር በፀሐይ ኃይል ታግዘው ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ የአየር ሁኔታን በማስከተል ከባድ ዝናብ ሊያስከትል እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህም ሌላ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኃላ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆነው በሰነበቱት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቦታዎች ዝናብ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም አሁን እየታዩና ለወደፊት ከተተነበዩ የትንበያ መረጃዎች በመነሳት በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር የመጀመሪያ ሳምንት ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በሂደት መዳከም ያለበት ቢሆንም፡ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ የመዘግየት አዝማሚያ ሊያሳይ እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ ሁሉም <u>የትግራይ ዞኖች፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ የጋምቤላ ክልል፤ የአማራ ክልል፤ ከአፋር ክልል ዞን 3 እና 5፤ ከኦሮሚያ ክልል ሁሉም የወለጋና የሸዋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ቡኖ በደሌ፣ የአርሲ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ አብዛኛዉ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እና የሲዳማ ክልል ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡</u>

ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 31/2022 ድረስ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.




## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የሴፕቴምበር ወር የመኸር ሰብል አምራች በሆኑትም ሆነ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች የእርጥበት ሁኔታው ጥሩ እንደሚሆንና በተለይም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ጥንካሬና የተስፋፉ እርጥበት እንደሚኖራቸው ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቀጣይ ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ ገንቢ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል። በተለይም ዘግይተዉ ለተዘሩና በእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙትም ሆነ ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉት ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውኃ አቅርቦት እንዲሁም የሚጠበቀው ቀጣይነት ያለው የእርጥበታማ ሁኔታ በክረምት ወቅት መጨረሻ በአፈር ውሰጥ በተከማቸው እርጥበት በመታገዝ በደጋማው አካባቢ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእፅዋት ልምላሜና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት መሻሻል በመጠኑ አነስተኛ ቢሆንም፣ ወደ ደቡብ እንደሚሰፋፉ የሚጠበቀው እርጥበት ባለፉት የክረምት ወራት በመደበኛ ሁኔታ ደረቅ ሆነው በሰነበቱትና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ለሆኑት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የጎላ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ በሌላም በኩል ከክረምት ዝናብ መጠናከር ጋር ተያይዞ በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ አካባቢዎች እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ስለሚችል ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም ከሰብል ጥበቃ አንፃር ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት

ጋር ተዳምሮ ለፀረ ሰብል ተባይ አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር ስለሚችል የሚመለከተው አካል የማሳ ጉብኝት በየጊዜው በማድረግ በመከታተል አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ በመጠቀምና ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በረባዳማ፣ ውሃ ገብና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሳዎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል በተጠቀሱት አከባቢዎች በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚኖርባቸው እንመክራለን።

## ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 30/2022 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የሴፕቴምበር ወር በፀሐይ ኃይል ታግዘው ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ነጎድጓዳማ የአየር ሁኔታን በማስከተል ከባድ ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህም ሌላ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኃላ እርጥበት ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆነው በሰነበቱት የመካከለኛውና የታችኛው የኦሞጊቤ እንዲሁም የስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ላይ እንደሚጠናከሩ ስለሚጠበቅ፤ የደቡብ የመካከለኛውና የታችኛው ገናሌዳዋ እና ዋቤሸበሌ ተፋሰሶች እርጥበት ማግኘት ይጀምራሉ፡፡ ይህንን ሁኔታ ተከትሎ በአብዛኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የታችኛው አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ እንዲሁም የላይኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከበጣም ከፍተኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ገናሌዳዋ፣ በጥቂት የታችኛው ስምጥሸለቆ እንዲሁም የመካከለኛውና የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህንን ሁኔታ ተከተሎ ከላይ በተጠቀሱት ከከፍተኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት መጠንና ስርጭት የሚኖራችው ተፋሰሶች ላይ የሚከሰተው ዝናብ በተዳፈት ቦታዎች ላይ መሬት መንሸራተት፣ የወንዞችና የውሃ ማጠራቀሚያዎች ሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ አካባቢዎች ላይ ደግሞ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል በእነዚህ ቦታዎች ላይ የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን ክትትልና ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እንመከራለን፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ ሆነዉ እንደሚቆዩ ይጠበቃል።